EVALUATION
DEPARTMENT

ግምገማዉ ገዢ ቁም ነገሮች//ሪፖረት 2/2015

Norad



# ኖርዌይ በልማት ትብብር /ዴቬሎፕመንት ኮኦፕሬሽን/ የሴቶች መብትና የጾታ እኩልነትን መሰረት አድርጋ የምትሰጠውን ድጋፍ በተመለከተ የተደረገ ግምገማ – *ኢትዮጵያን በተመለከተ የተካሄደ ዝርዝር ጥናት እንዲሁም የኔፓልንና የሞዛምቢክን ዝርዝር ጥናትና የግምገማ ማጠቃለያ ሪፖርት*

ይህ ሪፖርት ኖርዌይ ስለሴቶችና ልጃገረዶች መብት እንዲሁም ስለ ሥነጾታ እኩልነት አስመልክቶ በልማት ትብብር በኩል እ/ኤ/ላ ከ2007 እስከ 2015 ለኢትዮጲያ የሰጠችውን እገዛ ግምገማ ይመለከታል፡፡ ይህ ከሶሥቱ አገር አቀፍ ጥናቶች ውስጥ (ኔፓልንና ሞዛምቢክን ያካተተ) አንዱ ሲሆን ሰፋ ያለው የኖርዌይ እገዛ ውጤት ግምገማ አካል ነው፡፡ ግምገማው በፕሮጀክቱ የተገኙት ውጤቶች በኖርዌይ የሴቶች መብትና ፆታ እኩልነት በልማት ትብብር የትግበራ ዕቅድ (ሥነጾታ ትግበራ ዕቅድ) ውስጥ ትኩረት ከተሰጣቸው 4 ወሳኝ ነጥቦች ጋር ተያያዥነታቸውን ግምት ውስጥ ያስገባ ነው፡፡ እነዚህም 4 ነጥቦች ሴቶችን በፖለቲካዊና ኤኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ማብቃት፣ የፆታና ስነተዋልዶ መብቶች እና በሴቶች ላይ የሚደርስ ጥቃትን/ትንኮሳን ይመለከታል፡፡ ግምገማው 4 ሰፋ ያሉ ጥያቄዎችን ያካትታል፤

**ኮሚሽን ኤጀንት፡** ኖራድ የግምገማ ዲፓርትመንት

**የግምገማ ቡድን፡** የስዊድን ህዝባዊ አስተዳደር ኢንስቲትዩት፣ ከኦቨርሲስ ልማት ኢንስቲትዩቱና ከChr. Michelsen ኢንስቲትዩቱ ጋር በመተባበር

ODI ለኢትዮጲያው ጥናት ሃላፊነት ወስዷል፡፡ የዚህ የኢትዮጲያ ሪፖርት አቅራቢዎች ኒኮላስ ጆንስ (የቡድኑ መሪ)፣ ታቪሺ ጉፐታ፣ እና በቀለ ተፈራ ናቸው

1. ***ውጤታማነት፡*** ይህ የኖርዌይ የሴቶች መብትና የፆታ እኩልነት ድጋፍ የተጠበቀውን ውጤት በምን ያህል ደረጃ ማስፈጸም ችሏል?

2. ***ተያያዥነት/ተዛምዶ፡*** የኖርዌይ የሴቶች መብትና የጾታ እኩልነት ድጋፍ ከስነ ጾታ ትግበራ ዕቅድ ጋር ምን ያህል ተያያዥነት ነበረው ?

3. ***ተገቢነት፡*** ከኢትዮጵያ ሃገራዊ ቅድሚያዎች፣ ፍላጎቶች እና ሊተገበሩ የሚችሉ ክስተቶች ጋር ሲተያይ የኖርዌይ ድጋፍ ምን ያህል ተገቢነት ነበረው?

4. ***ዘላቂነት፡*** ይህ የኖርዌይ ድጋፍ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ በሆነ ሁኔታ ሀገራዊ የሴቶች መብትና የጾታ እኩልነት ሂደቶችን በማሻሻል ፣ እንዲሁም የዚህን ጉዳይ ሀገራዊ ባለቤትነት ከማጠናከር አንፃርና ወይም የሚመለከታቸውን ሃገራዊ ተቋሞችና አስፈጻሚ አጋሮች አቅም ከማጎልበት አንጻር ምን ለውጥ አምጥቶአል?

**የግምገማ ቡድኑ አቀራረብ**

ይህ ኢትዮጲያ ተኮር ጥናት 2 ዋና ነጥቦችን አካቶአል፤ 1) በዘውዳዊ ኖርዌይ ኤምባሲ ፕሮግራም ፖርትፎሊዮ ውስጥ የሚገኙ ከሴቶችና ልጃገረዶች መብቶችና ከሥነጾታ እኩልነት ጋር የተያያዙ ዘገባዎችንና መዛግብቶችን ክለሳ፣ እንዲሁም 2) በጾታና የሥነተዋልዶ ጤና መብትና በሴቶች ላይ ስለሚካሄድ ትንኮሳ አስመልክቶ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገባ ጉዳዮች ላይ የሚሰሩ ሁለት ፕሮግራሞች ላይ ጠለቅ ያለ ትንተና ናቸው ፡፡

የመጀመሪያው ፕሮግራም በኖርዌይ ቤተክርስትያን እርዳታ እና በዓለም አቀፍ ሴቭ ዘ ችልድረን የሚተዳደር ሲሆን የተቀረጸው የሴቶች ግርዛትን እንዲሁም

ጎጂ ባህላዊ ድርጊቶችን ለመቅረፍ ነው፡፡ የዚህ ፕሮግራም ትኩረት የኖርዌይ ቤተክርስትያን እርዳታ ተባባሪ /አጋር/ ድርጅት ከሆነው በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል በከምባታና ወላይታ ዞን የሚገኘው KMG ሥራዎች ጋር የታያያዘ ነው፡፡ ሁለተኛው ፕሮግራም ደግሞ በተባበሩት መንግሥታት የህዝብ ፈንድ/ (UNFPA) / እና በዩኒሴፍ / UNICEF/ ጥምረት የሚተዳደር ሲሆን በአማራና በኦሮሚያ የሚገኙ ሦስተኛ ደረጃ ተማሪዎች ስለ ጾታዊና የሥነ ተዋልዶ ጤና መብታቸው እገዛ የሰጠ ነው፡፡

የግምገማ ቡድኑ በሃገራዊ ደረጃ፣ በወረዳ ደረጃ እንዲሁም በቀበሌ ደረጃ ከሚገኙ የመንግሥት ቢሮዎች ከሚገኙ የሚመለከታቸው አካላትና ፕሮጀክቱን አስፈጻሚ ሠራተኞች የሆኑ ቁልፍ መረጃ ጠቋሚዎች ጋር ቃለ ምልልስ በማካሄድ ወሳኝ የሆኑ መረጃዎችን አሰባስቧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከፕሮግራሙ ተጠቃሚዎችና ሌሎች የማህበረሰቡ አባላት ጋር ጠለቅ ያለ ቃለ ምልልስና ቡድን ተኮር ውይይት በማካሄድ ከቁልፍ መረጃ ጠቋሚዎች የተገኘውን መረጃ የበለጠ አጠናክሮአል፡፡

የግምገማ ቡድኑ ትንተና ውጤቶችን በሦስት ደረጃዎች ለመለየት ጥሯል

***የስርዓት /ደንብ፣ሕግ/ ለውጥ፡*** የኖርዌይ ድጋፍ በሕግ/ በደንቦች፣ በዕርዳታ ደረጃ፣ ሀገር አቀፍ አመለካከቶች /ሕዝቡና ፖሊሲ አውጪዎች ስለሚነጋገሩባቸው ጉዳዮችና ማናቸውም ሃገራዊ በእንቅስቃሴ ላይ ያለ ሂደት/ ወይም የሴቶችን መብትና የጾታ እኩልነትን የበለጠ ሕጋዊነት ለመስጠት ምን ያህል አስተዋጾኦ አድርጎአል?

***የፕሮጀክቱ ውጤቶች፡*** ሴቶችንና ልጃገረዶችን ከማብቃት አንፃርና፣ ሕዝቡም ሆነ የማሕበረሰቡ ጉዳዮች ላይ ወሳኝ አካላትና የሃይማኖት መሪዎች ስለሥነ ጾታ እኩልነት ስላላቸው ባህሪና አመለካከት ለውጥ ማምጣት በተመለከተ ይህ የኖርዌይ ዕርዳታ ምን አስተዋጽኦ አድርጎአል?

***ድርጅታዊ ለውጥ፡*** ይህ የኖርዌይ ድጋፍ የአጋር ድርጅቶችን/ የመንግሥት ኤጀንሲዎች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ሲቪል ማሕበረሰቦች፣ የተባበሩት መንግሥታት ኤጀንሲዎች፣ እና የግል ድርጅቶች/ በሴቶች መብትና በሥነ ጾታ እኩልነት ስራዎችን እንዲሰሩ ምን ያህል የአቅም ግንባታ አካሂዷል?

ለግምገማው ሂደት ከተሰጠው የጊዜ ክልል አንፃር ቡድኑ ያተኮረው ጉልህና ተጨባጭ ለውጦችን መለየት ላይ ነው፡፡ ከሴቶች መብትና የሥነ ጾታ እኩልነት ለውጥ ሂደት ውስብስብነትና በተለያዩ ይዘቶች ውስጥ የተካተተ ከመሆኑ አንጻር የረዥም ጊዜ ለውጦችን መለየት አዳጋች ነው፡፡

## ሃገራዊ ይዘት

ባለፉት 10 ዓመታት ምንም እንኳን ሃገሪቱ በጠንካራ የኤኮኖሚ ዕድገት ላይ ብትሆንም፤ ኢትዮጲያ አሁንም ከዓለም ድሃ አገሮች አንድዋ ነች፤ በ Human Development Index መግለጫ አንጻር ከ187 አገሮች 173ኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች፡፡ በሌላ በኩል የሥነ ጾታ እኩልነትን ለመዋጋትና ሴቶችንና ልጃገረዶችን ማብቃትን ከማጠናከር አንጻር ሕጋዊና የፖሊሲ ለውጦች ባለፉት 20 ዓመታት ለልጃገረዶች ትርጉም አዘል መሻሻሎች እንደ የትምህርትና የመጀመሪያ ደረጃ ጤና እንክብካቤ፣ እናታዊና የስነተዋልዶ ጤና አገልግሎት ለውጦች ታይተዋል፡፡ ይህም ሆኖ የስነ ጾታ ልማት ማውጫ / Gender Development Index (2013) / የኢትዮጲያ ሴቶችና ልጃገረዶች አሁንም ያልተመቻቹላቸው ወሳኝ ነገሮች እንዳሉ ያሳይና አገሪቱን ከ187 ሀገሮች 129ኛ ደረጃ ላይ ያስቀምጣል፡፡ አድሎዋዊ የሆኑ ማህበረሰባዊ ልማዶች የሴቶችንና ልጃገሮዶችን ምርጫዎችንና አቅሞችን ይገድባሉ፡፡ ይህን በተመለከተ የ OECD ማህበረሰባዊ ተቋም እና Gender Index (2012) አገሪቱን ከ86 አገሮች 64ኛ ደረጃ ላይ አስቀምጠዋታል፡፡

ኖርዌይ ከኢትዮጲያ ጋር በፖለቲካ፣ የጋርዮሽ ዕርዳታ እንዲሁም በሚሲዮናዊ ሥራ የረጅም ጊዜ ታሪክ ያላት ሀገር ናት፡፡ ኢትዮጲያ ላለፉት ቅርብ 10 ዓመታት የኖርዌጂያን ዕርዳታ ቀዳሚ ተጠቃሚ አገር ሆና ቆይታለች፤ በ 1997 በተካሄደው ሀገርአቀፍ ምርጫ በተፈጠረው የሰብዓዊ መብት ጥሰት አስመልክቶ ትብብሩ ማሽቆልቆል ቢታይበትም፤ ሁለቱም ህገሮች ግንኙነታቸውን ከዚያም ወዲህ አጠናክረው ይገኛሉ፡፡ ኖርዌይ ከአራቱ ዋና የ OECD የልማት አጋዥ ኮሚቴ አገሮች / Development Assistance Committee (DAC) countries/ አንድዋና ከ2013 እ/ኤ/ኣ ጀምሮ በግምት እስከ 120.5 ሚሊዮን ዶላር የለገሰች ሀገር ነች፡፡ በኖርዌይ መንግሥት ከ እ/ኤ/ኣ 2007 እስከ 2013 በ Official Development Assistance (ODA) ከሚታገዙ ከ1050 ጠቅላላ ፕሮጀክቶች ውስጥ ከፍተኛውን ቁጥር (346) የያዙት ጤናና ማህበረሳባዊ አገልግሎት ላይ ያተኮሩት ሲሆኑ ፤ (225) መልካም አስተዳደር ላይ ፤ 197 ፕሮጀክቶች ደግሞ ለኤኮኖሚያዊ ልማትና ንግድ ትኩረት የሰጡ ናቸው፡፡ ሆኖም የኖርዌይ ሴቶች መብትና ሥነ ጾታ ላይ ያተኮረ ፕሮግራም ለኢትዮጲያ ዕርዳታ ከአጠቃላይ የሀገሪቱ የውጪ ዕርዳታ 32 መቶኛውን ይይዛል፡፡ (ለ DAC's Creditor Reporting System የሚቀርቡ የዕርዳታ ሥራ ሪፖርቶች የስነ ጾታ እኩልነትን ዋና ዒላማ ያደረጉ መሆን አለመሆናቸውን ማመላከት ይኖርባቸዋል፤ እናም ይህ ሥነ ጾታ ላይ ያተኮረ ዕርዳታ ተብሎ የተገለጸ ነው)፡፡ ከሌሎች የ OECD ለጋሽ አገሮች ጋር ሲነፃፀር ኖርዌይ ሥነ ጾታ ተኮር ዕርዳታን በተመለከተ ከ13 አገሮች 12ኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች፡፡

ከሌሎቹ ሁለቱ አገር አቀፍ ጉዳይ ተኮር ጥናት (ሞዛምቢክና ኔፓል) ጋር ሲነጻጸር፤ በኢትዮጲያ የሚገኘው የኖርዌይ ኤምባሲ የሴቶችና የሥነ ጾታ እኩልነት ዕርዳታን ተግባር ላይ ያዋለው በትንሹ ነው፡፡ ይህ ፈንድ የተመደበው በሌሎች ሴክተሮች በጀት መስመር ፈንድ ማግኘት የማይችሉትን እንደ በሴቶች መብትና በሥነ ጾታ እኩልነት ላይ ፕሮግራሞችን ለመጀመር፣ ትንተናዊና ዓቅም ማጠናከሪያ ስራዎችን ለማካሄድ ነበር፡፡ በኢትዮጲያ የኤምባሲው ስትራተጂ ሥነ ፆታና ተያያዥ ጉዳዮችን በሴክተር በጀት ወይም በጠቅላላ የፈንድ ስርጨት መስመር ሥር ለማገዝ ነበር፡፡

## ቁልፍ ግኝቶች

በአጠቃላይ ሲታይ ኖርዌይ በኢትዮጲያ የሴቶችን መብትና የሥነ ጾታ አኩልነትን ለማሻሻል አዎንታዊ አስተዋጽኦ አድርጋለች፡፡ ነገር ግን ከሥራዎቹ





የተገኙትን ለውጦችና ልገሳውን ለማጠናከር የለውጦቹ ተገቢነት፣ ውጤታማነትና ዘላቂነት በተመለከተ፣ ብዙ ስራዎች ይቀራሉ፡፡

### ተገቢነት

- ኖርዌይ የኢትዮጲያ ሴቶች መብታቸውን እንዲያስከብሩ ጠቃሚ ነገር ግን መሃከለኛ የሆነ ሚና ተጫውታለች፡፡ የሥነ ጾታ ዝርጋታና የሴቶች መብት ጥያቄዎች በሃገራዊ አጀንዳዎች እንዲሁም በመልካም አስተዳደር፣ በኤነርጂ፣ በአየር ጠባይ ለውጥ እና በግብርና ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች እንዲካተቱ አድርጓል፡፡ የአየር ጠባይ ለውጥ ፕሮግራም ዘርፍ በሥነ ጾታ እኩልነት ላይ ሃገራዊ ውይይት እንዲካሄድ ያገዘ ሲሆን፤ እንዲሁም በተወሰነ ደረጃም ቢሆን በዚህ ዘርፍ የመንግሥታዊ አጋሮችን አቅም አጎልብቷል፡፡ በመንግሥት ቅድሚያ የሚሰጣቸው ፕሮግራሞች ጋር ተያያዥነት ያለው የዘላቂ ግብርና እንቅስቃሴም ምንም እንኳን ሽፋኑ መጠነኛ ቢሆንም ሴቶችን በተለይም በዓቅም ግንባታ ረገድ አካቷል፡፡

- መልካም አስተዳደርን በተመለከተ የኖርዌይ ድጋፍ የሴቶች ግርዛትንና ጎጂ ባህላዊ ድርጊቶች የአገር አቀፍ ፖሊሲ ጉዳዮች አጀንዳ ውስጥ እንዲካተቱ ትልቅ ሚና ተጫውቷል፡፡ የኢትዮጲያ መንግሥት እ/ኤ/ኣ በ2025 የሴት ግርዛትን በአጠቃላይ ለማስወገድ ቃል መግባትን በተመለከተ የኖርዌይ ድጋፍ ከፊል እጅ አለበት፡፡

- የኖርዌይ ድጋፍ አጋር በሆኑት በ UNICEF/UNFPA ጥምር ፕሮግራም (በተለይ በሦስተኛ ደረጃ) የሚካሄደው ወጣት ተኮር ወሲባዊና የስነተዋልዶ ጤና አገልግሎት የትምህርት ሚኒስቴር ለተጎጂ ወጣት ሴቶች ድጋፍ ለመስጠት ካስቀመጠው ግብ ጋር በቅርብ የተሳሰረ ነው፡፡

- እ/ኤ/ኣ በ 2009 የወጣው የCSO (የሲቪል ማሕበረሰብ ደርጅት) ሕግ በተለይ ደግሞ በሰብአዊ መብትና የሴቶች መብት ላይ ለሚሰሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከፈጠረባቸው ገደብ፣ ቁጥጥርና ግዴታ አንጻር በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሚገኘው የሰብዓዊ መብት ማዕከል በኖርዌይ የሚሰጠው ድጋፍ ሊመሰገን የሚገባው ነው፡፡ ይህ ድጋፍ ከዚህ በፊት በሴት ጠበቃዎች ማህበርና በአንዳንድ ሲቪል ማህበረሰብ ቡድኖች ብቻ ተይዞ የነበረውን የአገልግሎት ክፍተት እንዲሟላ አድርጓል፡፡

### ውጤታማነት

- ***በሲስተም ደረጃ ለውጦች አኳያ፣*** የሴቶች ግርዛትን ከመከላከል አንጻር የኤምባሲው ድጋፍ የሚመሰገን ነው፡፡ ማህበራዊ ደንቦች ላይ ለውጥ ማምጣት ውስብስብና ቀጥተኛ ያልሆነ እንደሆነ በመገንዘብ የኤምባሲው የረጅም ጊዜ ድጋፍ ይህ ጉዳይ በሃገራዊ አጀንዳ ላይ እንዲቀርብ ወሳኝ ነበር፡፡ ጉዳዩ በሃገራዊ የልማት ዕቅዶች መካተት ብቻ ሳይሆን በሃይማኖት ተቋማት የቃል መግለጫ ጽሁፎችም ውስጥ መካተት ችሏል፡፡ ኖርዌይ የሥነጾታ ጉዳይ በአየር ንብረት ለውጥ ላይ በሚካሄዱ የፖሊሲ ምክክሮች እንዲካተት መጠነኛ ቢሆንም ጠቃሚ ሚና ተጫውታለች፡፡

- ***በፕሮጀክት ደረጃ ከሚታዩ ለውጦች አንጻር፡*** የግምገማ ቡድኑ ሁለቱ ፕሮግራሞች በኢትዮጲያ ልጃገረዶችና ወጣት ሴቶች ላይ አዎንታዊ የህይወት ለውጥ እያመጡ መሆኑን አረጋግጧል፡፡ ግምገማው የዳሰሳቸው ጥንካሬዎችና ክፍተቶች ወይንም ድክመቶች ደግሞ ከዚህ በታች ተካተዋል፤

- ***ጥንካሬ፡*** የሴቶችን ግርዛት ለማስወገድ የሚንቀሳቀሰው ፕሮግራም ስራውን የሚሰራው በጣም ከተገለሉ ቡድኖች ጋር (ገራዦች፣ አይነኬ የማህበረሰብ ቡድኖች፣ ልጃገረዶች) ሲሆን ይኸውም በአካባቢው ከሚገኙ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በጋራ በመስራት የማህበረሰብ ውይይት በማካሄድ ግንዛቤ በመፍጠር ነው፡፡ በከምባታ ጎልማሳና ወጣት ወንዶች የማህበረሰብ ደንቦች ላይ ለውጥ እንዲያመጡ እንዲሁም ያልተገረዙ ልጃገረዶች ክበብ በትምህርት ቤት በመመስረት ልጃገረዶችን የማብቃት ስራ ይካሄዳል፡፡

- ለ‹ሦስተኛ ደረጃ› ተማሪዎች ጾታዊና የስነተዋልዶ ጤና መብት አቅርቦት የሚሰጠው ፕሮግራምን በተመለከተ በየካምፓሱ የታዩ የአገልግሎት ክፍተትና የተማሪዎች ተጋላጭነት ነጥቦችን አንስቷአል፡፡ እንዲሁም ለተቸገሩ ተማሪዎች የገንዘብ እገዛ ያደረገ ሲሆን፤ በሌላ በኩል ተጋላጭ ለሆኑ ወጣት ሴቶች የገቢ ማስገኛ ስራዎችም እገዛ ሰጥቷል፡፡ ት/ቤትን መሰረት ያደረገ የልጃገረዶች ክበብን በተመለከተ የዩኒቨርስቲ ክበቦች ወጣት ሴቶች ስሜታቸውን በነፃነት የሚወያዩበትና ክህሎታቸውን የሚያዳብሩበት ደህንነቱ የተጠበቀ ቦታ አዘጋጅተው ሰጥቷል፡፡

- ***እጥረት፡*** የሴቶች ግርዛት መከላከል ፕሮግራም ወደ ጎረቤት ወላይታ ዞን ስራውን ከማስፋፋቱ በፊት በከምባታ ዞን በነበረው ተሳትፎ የትኞቹ ወሳኝ ሂደቶች አዎንታዊ ለውጥ እንዳመጡ የመረዳቱና ትኩረት መስጠቱ አናሳ ነበር ። እንዲሁም በወላይታ ስለሚካሄደው የሴቶች ግርዛት ልማድና ዝንባሌ የተካሄደው አሰሳ ውስን ነበር፡፡ በሁለቱም ዞኖች ሥራ ላይ የዋለው ሞዴል ተመሳሳይ ነበር፡፡ ከአካባቢው ሁኔታዎችና ክስተቶች ጋር ፕሮግራሙን ለማቀናጀት የነበረው ጥረት አነስተኛ በመሆኑ በወላይታ የተገኘው ውጤት አነስተኛ ነበር፡፡ በተጨማሪ ፕሮግራሙ በከምባታ የሴቶች ግርዛትን ለማስወገድ አስደናቂ መንገዶችን የከፈተ ቢሆንም፤ ስለማህበራዊ ደንቦች ለውጥ ቀጥተኛ ያልሆነ ተፈጥሮአዊ ሁኔታን አስመልክቶ ውስን የሆነ ግንዛቤ በወላይታ ካጋጠመ ክስተት ጋር ተዛምዶ መሄድ አልቻለም፤ እንዲሁም ከጊዜ ጋር የሚመጡ ለውጦችን ትኩረት አልሰጠም፡፡ ለአብነት ያህልም ምንም እንኳን ያልተገረዙ ልጃገረዶች በወላይታ አብላጫውን ቁጥር ቢይዙም የተመሰረቱት ክበቦች በወጣት ወንዶችና በወጣት ልጃገረዶች መሃከል ሰፋ ያለ ጥምረት በመፍጠር ፋንታ ያቀፉትና በስራ ያሰማሩት እነዚህን ልጃገረዶች ብቻ ነበር፡፡

- ሁለተኛውን ፕሮግራም ካሰናከሉ ድክመቶች ውስጥ ውስን የሆነ የፆታዊና የሥነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎትና አቅርቦት እንዲሁም ተአማኒነትን ለመፍጠር የትኩረት እጥረት ይገኙበታል፡፡ በተጨማሪ የአገልግሎትና የድጋፍ ቡድኖች የሆኑት ክበቦች የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ያገለሉ ይመስላሉ፡፡ ምክንያቱም እነዚህ አካልጉዳተኛ ተማሪዎች ለእነርሱ የተለየ መታጠቢያ ክፍሎችና ሌሎች



የሚያስፈልጓቸው አገልግሎቶች አለመሟላታቸውን ሪፖረት አድርገዋል፡፡ በሌላ በኩል የገቢ ማስገኛ ሥራዎች ተሳታፊዎችን የመለየት ስራ ላይ ድክመት ታይቶበታል። ይኸውም ተጋላጭ ወጣት ሴቶችንም ሊያካትት ሲገባ ዒላማ አድርጎ የሰራው በዕድሜ የገፉ እናቶችን ብቻ ተጠቃሚ በማድረግ ነበር፡፡

- ***ያልተጠበቁ ክስተቶች፡*** ግምገማው በሁለቱም ፕሮግራሞች አዎንታዊና አሉታዊ የሆኑ አንዳንድ ያልተጠበቁ ክስተቶች እንደተከሰቱ አሳይቷል፡፡ ለምሳሌ የሴቶች ግርዛትን የሚቃወመውን ሕግ በማህበረሰብ አቀፍ የግንዛቤ ማሰጨበጫ ስራ ለማስተዋወቅ የተካሄደው ጥረት በማህበረሰቡ ዘንድ ስጋት እየፈጠረና ወደ ያልተጠበቀ አዝማሚያ እየወሰደ ነው፡፡ አንዳንድ ወላጆች (በተለይ በወላይታ ዞን) ድርጊታቸው እንዳይታወቅባቸው ሴት ልጆቻቸውን ቀድሞ ይገርዙበት ከነበረው እድሜ አስቀድመው ለመግረዝ እየወሰኑ ነው፡፡ የግርዛት ሂደቱን ለማስቆም የሚደረገው ጠንካራ ጥረት ድርጊቱ በድብቅና ውስጥ ለውስጥ እንዲካሄድ አስትዋፅዎ እያደረገ ነው፡፡ ድርጊቱ መፈጸሙን መረጃ የሚያቀብሉት ላይም እየተወሰደ ያለው የተገላቢጦሽ አመጽ (አንዳንዴ ቁጣ አዘል) ለፕሮግራሙ ግልፅ ዓደጋ እየሆነ ነው፡፡ በተጨማሪ በተለያዩ ፕሮግራም የሚፈፀምባቸው ቦታዎች ላይ ለዕድሜ ልዩነት በቂ ትኩረት ባለመሰጠቱ በወላይታ ዞን ያልተገረዙ ሴቶችን ቡድን ክበብ ለመመስረት የተደረገው ጥረት (በወላይታ ገና በትንሽ ዕድሜ ስለሚገረዙ) አንዳንድ ወጣት (ያልተገረዙ) ልጃገረዶችን መጥፎ ስም እያሰጠ ይገኛል፡፡

- የ UNFPA/UNICEF ጥምር ፕሮግራምን በተመለከተ (አዳማ ዩኒቨርስቲ) ተማሪዎቹ ከፕሮግራሙ ድጋፍ ያገኛሉ በሚል ሰበብ አንዳንድ የተማሪ ወላጆችና ሌሎች የቤተሰብ አባላት ቀድሞ ለነዚህ ተማሪዎች ይልኩላቸው የነበረውን ድጋፍ አቁመዋል፡፡ ሆኖም ከፕሮግራሙ የሚሰጠው እገዛ ጥቂት ስለሆነ የቤተሰብ ዕርዳታ መቋረጥ በተማሪዎቹ ላይ የተገላቢጦሽ ችግር እየፈጠረ ነው፡፡ በተጨማሪ ፆታዊና የሥነተዋልዶ ጤና አገልግሎት የሚሹ ወጣቶች አገልግሎቱ ላይ እምነት እንዲኖራቸው የሚደረገው ጥረት አናሳ ስለሆነ የስራው ሂደት የሚያስከትለውን አደጋ በመስጋት ይህን አገልግሎት እየተጠቀሙ አይደለም፡፡

› ***በድርጅት ደረጃ ለውጦችን በተመለከተ፡*** የኤምባሲው ሚናና ውጤቶች መጠነኛ ናቸው፡፡ ኤምባሲው ለማዕድን ሚኒስቴር የሥነ ጾታ ዕቅድ ለማውጣትና እንዲሁም ጅማሬው ላይ ቴክኒካዊ ለአጭር ጊዜ ቢሆንም ድጋፍ ሰጥቷል ፡፡ ሌሎች ለጋሾች ሌላ የእገዛ መንገድ በሚያፈላልጉበት ሰዓት ኤምባሲው ለተባበሩት መንግሥታት/ UN / ቀጣይ ድጋፍ ለመስጠት ጥሯል፡፡ ሆኖም በቂ ክትትል ስላልተካሄደ ይህ ድጋፍ የኤምባሲው ማኔጅመንት ሌላው ቢቀር ከ UNFPA, UNICEF እና UNWOMEN ጋር ከሰራው ስራ አንጻር ሊፈጠር ያሰበውን‹የወሳኝ ጓደኛ› ሚና ማሟላት አልቻለም ፡፡ በመጨረሻም ምንም እንኳን ኤምባሲው በጣም ተፈላጊ የሆነ ሃብት ለሀገር በቀል NGOs/ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች/ ሥነ ጾታ ተኮር ስራ እንዲቀጥሉ እያቀረበ ቢሆንም ጠንካራ ክትትል፣ ግምገማና መማማር ለማረጋገጥ የቴክኒካዊ ድጋፍ ውስን መሆን ይህ ሃብት ለበለጠ ጥቅም እንዳይውል አድርጎታል፡፡

- ጠንካራ ውጤቶች እንዳይመዘገቡ ያደረጉ ተግዳሮቶች ከብዙ ነገሮች ጋር ሊያያዙ ይችላሉ፡፡ አንዱ ችግር የሰብዓዊ መብትና የሥነጾታ እኩልነት ፕሮግራም አፊሰሩን ሚና ሰፋ ያለ የማቀናጀት ስራ በማካሄድ ፈንታ አጥቦ ውስን የፕሮጀክቱ ስነጾታና ማህበረሰባዊ መብቶች ጉዳዮች ላይ ብቻ ያተኮረ መሆኑ ነው፡፡ ሌላው ችግር ማኔጅመንትና ሰራተኛው በተመሳሳይ አጠቃላይ አመለካከት መያዝ ይኸውም ስነጾታን የተለየ ትኩረት ባለመስጠት ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገባ ተወዳዳሪ ነጥቦች ውስጥ እንደ አንዱ አድርጎ መወሰድ ሲሆን ሌላው ደግሞ የኤምባሲ ሰራተኛው ስነጾታን ትኩረት ሰጥተው በሚንቀሳቀሱባቸው የሥራ ዘርፎች ማቀናጀት እንዲችሉ ለኣቅም ግንባታ ስልጠና የሚውል መዋዕለ ንዋይ ውስን መሆን ነው፡፡ እነዚህ ድክመቶች ሥነ ጾታ ላይ በቂ ባልሆነ የሪፖርት ዘይቤ ምክንያትም ተባብሰዋል፡፡ የስነጾታ ፓይለት ሌጋሲ ደካማ መሆን እንዲሁም በሴቶችና ስነጾታ እኩልነት እርዳታ የተገኘን ዕድል ለመጠቀም የተካሄደ ጥረት ደካማነት ታይተዋል፡፡

## ዘላቂነት

› የሴቶች ግርዛት መከላከልን ፕሮግራም በተመለከተ የኖርዌይ የረጅም ጊዜ ፈንድ ድጋፍ ቃል መግባት ምንም እንኳን ከሌሎች ዋና ለጋሾች የተለየ ቢሆንም ዋነኛነቱን አረጋግጧል፡፡ በመተግበር ላይ ያለው የኤምባሲው ቀጣይ ድጋፍ የሚመሰገን ነው፡፡ ምክንያቱም ለውጡ ቀጥተኛ መስመር ይዞ የሚሄድ ሳይሆን ምናልባትም የሰዎች አመለካከትና ባህሪ የተገላቢጦሽ ለውጥም ሊፈጠር ይችላልና፡፡

› የስነጾታና የስነተዋልዶ ጤና መብቶችን በተመለከተ ከመንግሥታዊ ሀገራዊ ተቋማት ጋር መስራት እንደ መርህ የሚበረታታ ነው፡፡ ሆኖም በተግባር ሲታይ ደካማ የክትትል ስርዓት እና ውስን የሆነ ፈንድ ለወደፊት ዓቅምን የመገንባት ዕድልን ያሳጣል፡፡

› በኤምባሲ ደረጃ ኖርዌይ የሴቶች መብትንና የሥነጾታ እኩልነት የማበረታታት ጉዳዩ ላይ በቀጥታ እየሰሩ ያሉ ፕሮጀክቶችን የገንዘብ ድጋፍ ከመስጠት ውጪ የፖሊሲ ክርክሮች ውስጥ በመግባት ለውጥ ለማምጣት ያላት ዕድል ውስን ነው፡፡ የኤምባሲው ባልደረቦች በሁሉም ዘርፍ የስነጾታ ጉዳይን ያካትቱ ዘንድ የዓቅም ግንባታ ለመስጠት የተደረገው ጥረትም አናሳ ነው፡፡ በፕሮጀክቶች ሥነ ጾታን ለሚያካትቱ የሚሰጥ ማበረታቻ የለም፤ እንዲሁም በእያንዳንዱ ፕሮጀክት የሥነጾታ ይዘት ላይ የሚካሄድ የተሰጠና ጠለቅ ያለ ውይይት የለም፡ ፡ ይህን ክስተት ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና ለተባበሩት መንግሥታት አጋሮች ጠንካራ ግምገማና ከግምገማው የመማር ሂደት እንዲካሄድ የሚሰጥ ድጋፍ አለመኖሩም ይበልጥ አባብሶታል ማለት ይቻላል፡፡ ውጤቱ ደግሞ ‹ጥቅል› የሆነ ፕሮግራምና ከዚህ በበለጠ ወጥ የሆነ ስርዓት አዘልና ወጪ ቆጣቢ በሆነ ሁኔታ ሊካሄድ ሲገባ ዝቅ ባለ ሁኔታ እየተተገበረ ያለ ፕሮግራም ይሆናል፡፡ ይህ ደግሞ ውሎአድሮ የኤምባሲውን ዘላቂ፣ ከፍተኛ ለውጥ አምጪ የፕሮግራም ሞዴሎችንና እርምጃዎችን የመለየት አቅሙን ይገድባል፡፡



## ምክረ ሃሳብ

የግምገማ ቡድኑ ዋና ምክረ ሃሳብ የኖርዌይ ልማት ትብብር በዋነኝነት ለወቅቱ ሥራዎች ትኩረቱ ይበልጥ ስትራተጂያዊ አቀራረብ ይሆን ዘንድ ነው፡፡ ማኔጀሮችና አማካሪዎች ካለባቸው የሥራ ብዛት አንጻር የጊዜ እጥረት እንዳለባቸው እንረዳለን፡፡ ሆኖም መረጃዎች የሚያሳዩትና የሚጠቁሙት ይበልጥ ስትራተጂያዊ አቀራረብ መጠቀም ያለውን ማነቆ በማስወገድ ጠንካራ ውጤቶች ማስመዝገብ እንደሚቻል ነው፡፡ በእርግጥ ይህን አሰራር ሥራ ላይ ለማዋል ተጨማሪ ሃብት ያስፈልጋል፤ ደግሞም ኖርዌይ ከሌሎች መሳይ ጓድ አገሮች ጋር ሲነጻጸር ለሥነጾታ ተኮር የምትሰጠው ዕርዳታ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ነው፡፡ ሆኖም ከተጨማሪ ሃብት ባሻገር ስትራተጂያዊ አቀራረብ ይበልጥ ከፍተኛ ለውጦችንና መሻሻሎችን ማስመዝገብ ያስችላል፡፡ የሚከተሉት ምክረ ሃሳቦች ኖርዌይ በኢትዮጲያ በምታካሂደው የሴቶችና ልጃገረዶች መብትና የሥነጾታ እኩልነት ላይ ያተኮረ የልማት ትብብር ለውጥን እንዴት ማጠናከር እንደሚቻል ሃሳብ ይሰጣሉ፡፡

***ሥነጾታን በዘርፍ ፕሮግራሞች ማካተት እንዲቻል ለአካባቢው የተስማማ የዓቅም ግንባታ ድጋፍ መስጠት፡*** ከአካባቢው የተስማማና አብሮ የሚሄድ የዓቅም ግንባታ ለተለያዩ ዘርፎች እንደ ኤነርጂ፣ ኤኮኖሚያዊ ልማት፣ መልካም አስተዳደርና የአየር ንብረት ለውጥ ለመሳሰሉት መስጠት ፕሮግራሞች በሥነጾታው ዘርፍ ይበልጥ ስትራተጂያዊና ሲስተም አዘል ትኩረት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ ኤምባሲው እንደ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ የ UN አካሎች፣ በክልል ደረጃ ያሉ የተለያዩ ሚኒስቴር መ/ቤቶች ጋር በአጋርነት የሚያካሂዳቸውን የሥራ ክንውኖቹን ይበልጥ ማጠናከርና ማሻሻል ከፈለገ ይህ የዓቅም ግንባታ ወሳኝ ነው፤ ምክንያቱም እነዚህ የተጠቀሱት በሙሉ የሥነጾታ ጉዳይን ይተገብሩ ዘንድ ይህን ድጋፍ እጅጉን ይፈልጉታልና፡፡

***ኤምባሲው የሃብት ድጋፍ ለሰጣቸው ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች ጠንካራ፣ ነጻ፣ የለውጥ ግምገማ ምክር እንዲያገኝ ማስቻል፡*** በግምገማው ሂደት ፕሮጀክቶች ጥራት ላለው የፕሮጀክት ቀረጻ ደካማ ትኩረት፣ የመነሻ መረጃ አጠቃቀም ድክመት፣ የአማካይ ዘመንና የመጨረሻ ዘመን ግምገማ በተካሄዱባቸው ፕሮጀክቶች የተገኙትን ግኝቶች አጠቃቀም ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ይህ ደግሞ የኤምባሲው ባልደረቦች ውጤታማ ድጋፍ ለመስጠት አቅሙ የላቸውም ወይ ደግሞ ጊዜው የላቸውም እናም ልንማማርባቸው የሚገባ ዕድሎችን እያጣናቸው ነው፡፡ የባልደረቦችን ዓቅም ለማጎልበትና ጠንካራ የክትትልና የግምገማ ሥራዎችን እንዲያካሂዱ ለማድረግ ነጻና ውጫዊ ድጋፍ እንዲኖር ማድረግ ይገባል፡፡ ይህ ደግሞ በመካሄድ ያሉት የፕሮግራም ሥራዎች ተሸጋጋሪ ለውጥ እንዲያመጡ ያስችላቸዋል፡፡

***ማህበራዊ ለውጥን ይበልጥ መለካት የሚያስችሉ አመላካቾችን ሥራ ላይ ለማዋል ድጋፍ መስጠት፡*** ኤምባሲው በረጅም ጊዜ ድጋፍ ምስቅልቅል ማህበራዊ ልማዶች ባሉበት አካባቢ የባህሪና የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት የሚያደርገውን ጥረት መለካት የሚያስችሉ አመላካቾች ሥራ ላይ ሊያውል ይገባል፡፡ ይህ ደግሞ ሊሆን የሚችለው በሥነጾታ እኩልነትና ማብቃት የተገኙ ውጤቶችን ለማሳየት አንድ ወጥ ብቻ ሳይሆን የቅይጥ ዘዴዎችን ጠቃሚነት




የህጻናት አድን ድርጅትና የፖፑሌሺን ሚድያ ሴንትር የሴት ልጅ ግርዛትን ለማስቀረት ባደረጉት ዘመቻ ላይ የተጠቀሙበት ፖስተር



ስንረዳና የማህበራዊ ልምዶች ለውጥና የማብቃት ሂደት ተፈጥሮው ቀጥተኛ አለመሆኑን ስናስተውል ነው፡፡ ከ Norad ወይም ሌላ ሦስተኛ አካል ጋር በመሆን ኤምባሲው የሪፖርትና የግምገማ መሣሪያዎቹን ጠቃሚ በሆነ ሁኔታ ማስፋት ይችላል፡፡

***የሰብአዊ መብትና የሥነጾታ እኩልነት ፕሮግራም ኦፊሰር ሥነጾታ ጉዳይን በተመለከተ በተለያዩ ዘርፎች ሰፋ ያለና፣ የማቀናጀት ሚና እንዲጫወት ማስቻል፡*** ባሁኑ ሰዓት ሥነጾታ በኤምባሲው ዝቅ ብሎ ‹ከብዙ ስራዎች እንደ አንዱ› ብቻ ተቆጥሮ በቂ በሆነ ሁኔታ ቅድሚያ ተሰጥቶት አይታይም፡፡ ይህን ሁኔታ ለማስተካከል፣በተለያዩ ክፍሎች መጣጣምንና ልምድ ልውውጥን ለማበረታታት፣ ኤምባሲው ለስራው ወጪ የሚሆን ፈንድ በማዘጋጀት የፕሮግራም ኦፊሰሩ ደግሞ ሥነጾታ የበለጠ የስትራተጂ ትኩረት እንደተሰጠው ለማረጋገጥ ጠንካራ የማቀናጀት ሚና እንዲጫወት መደረግ አለበት፡፡

***ለሴቶችና ለሥነጾታ እኩልነት የተመደበውን ቀጥተኛ ድጋፍ የበለጠ ጥቅም ላይ ማዋል፡*** ኤምባሲው ለሴቶችና ሥነጾታ እኩልነት የተቀመጠውን ቀጥተኛ ድጋፍ እነዚህ ከላይ የተቀመጡትን ምክረ ሃሳቦች ተግባር ላይ እንዲውሉ ለማድረግ ሊጠቀምበት ይችላል፡፡ ወይንም ገዳቢ በሆነው ሃገር አቀፍ ሕግ ምክንያት ሀገር በቀል ድርጅቶች ከሌሎች ምንጮች ፈንድ ለማግኘት ትግል ላይ በመሆናቸው አዳዲስ ሃሳቦችን አቅራቢና በፈርቀዳጅ መብት ተኮር ጉዳዮች ላይ ለተሰማሩ አገር በቀል ድርጅቶች እገዛ እንዲውል ማድረግ ይቻላል ፡፡

ኢትዮጵያን በተመለከተ የተካሄደ ዝርዝር ጥናት እንዲሁም የኔፓልንና የሞዛምቢክን ዝርዝር ጥናትና የግምገማ ማጠቃለያ ሪፖርት ለማንበብ የሚከተለዉን ዌብሳት ይጎብኙ፡፡ http://www.norad.no/en/toolspublications/publications/2015/evaluation-of-Norways-support-to-womens-rights-and-gender-equality-in-evelopment-cooperation/

በኖርወይ የልማት ተራድኦ ዉስጥ የሚገኘዉ የግምገማዉ ክፍል በኖርወይ የርዳታ በጀት የሚነቀሳቀሱ የልማት ተግባሮች እንዲገመገሙ ያደርጋል፡፡ የግመገማ ክፍሉ በተሰጠዉ ልዩ አደራ የሚተዳደር ሆኖ ተጠሪነቱ በቀጥታ ለዉጭ ጉዳይ ሚኒስተሪ ነዉ፡፡ግመገማዎቹ በገለልተኛ ገምጋሚዎች የሚደረጉ ሆነዉ ሁሉም የግምገማ ዉጤቶች ለህዝብ ይፋ ይደረጋሉ፡፡


አክቶበር 2015
የኮፒ ብዛት፡100
ISBN: 978-82-7548-812-9
Photo: Nicola Jones



**Norad**
Norwegian Agency for Development Cooperation
www.norad.no
post-eval@norad.no